በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት

Ethiopian Meteorology Institute

ከኦክቶበር 11-20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ እና ከኦክቶበር 21-31 እና ከኖቬምበር 1-10/2026

የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2026

አዲስ አበባ

1. እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ፣ በመዕራብና በሰሜን ምስራቅ ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ37 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ ከነበረዉ ከባድ ዝናብ ጋር በተያያዘ በመልካ ዲዳ፣ በቀላፎ፣ በጎዴ እና በፋፌን አካባቢዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ተከስቷል፡፡

በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብና ደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40.0-73.2 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች አርባምንጭ 73.2፣ ጎዴ 68፣ መንደር11 63.5፣ አዴት 60፣ መርሳ 57.4፣ አቦሞሪንጋ 47.2፣ ዶሎመና 45.5፣ አታንጎ 45፣ ባምቢስ 43.5፣ ማጂቴ 42.8፣ ጊምቢ 41.5፣ ጋምቤላ 41.2፣ አባጃራ 41 እና በሽላቦ 40 ይገኙበታል፡፡



ምስል1: ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ፣ ነጎብ፣ እና ጃረር ዞኖች፤ የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ እንዲሁም የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ከሆኑ ዞኖች የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች፤ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፤ የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም እና የአዊ ዞኖች፤ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤የወላይታ፣ ጎፋ እና ጌድዮ ዞኖች ላይ ከ15-130 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተጨማሪም የሰሜን፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅ ጎጃም፤ የምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፤የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ቅልበቲ፣ ፋንቲ፣ ማሂ፣ ሃሪ፣ ጋቢ ዞኖች ከ5-30 ሚ.ሜ የሚደርስ ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ዝናብ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ኦኖች፤ ከሶማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ፣ ነጎብ፣ እና ጃረር ዞኖች፤ የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ እንዲሁም የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ከሆኑ ዞኖች የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ዞኖች፤ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፤ የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም እና የአዊ ዞኖች፤ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤የወላይታ፣ ጎፋ እና ጌድዮ ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡



ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

1.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፤ በደቡብ ምስራቅ፣ በምዕራብ አጋማሽ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በሰሜን መዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የአፈር ዉስጥ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል ጋር ተያይዞ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚኙት የረጅም ጊዜ ሰብሎችም ሆነ ለሌሎች የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ እንዲሁም በወቅቱ መጨረሻ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለተዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ላሉ ሰብሎች የውሃ ፍላጎ መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተገኘው እርጥበት ጥምር ግብርና ለሚያከናውኑ አካባቢዎች ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ነበረ። እንዲሁም በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ ቆላማው አካባቢ ለሚኖሩ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች በቂ የግጦሽ ሣርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 4)።

1.3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2026 የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው ዋቤ ሸበሌ፣ ኦጋዴን፣ ገናሌ ዳዋ፣ ባሮአኮቦ፣ በላይኛውና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ተከዜ፣ እንዲሁም አባይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት የነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በታችኛው ኦጋዴን፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በመካከለኛና ታችኛው ገናሌዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ባሮአኮቦ እና አባይ ተፋሰሶች ደግሞ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር ውኃ ነበረው፡፡ በመሆኑም ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት ግብዓት ጥሩ አስተዋፅዖ እንደነበረው የተተነተኑ የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በተለይም ዋነኛ ወቅታችው ለሆኑት ለአብዛኛው ዋቤ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን ለመካከለኛና ታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ ጠቀሜታው እጅግ የጎላ ነው (ካርታ 5)።



ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

2. እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በመጪዎቹ የኦክቶበር ሶስተኛዉ አሥራ አንድ ቀናቶች አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሳምንቱ አጋማሽ ጀምሮ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡

በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት የምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ፣ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት ደቡብ ምዕራብ እና ደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖረቸዋል (ካርታ 1)፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በሰሜን ምዕራብ እና በሰሜን የሀገሪቱ አከባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጥን ያለዉ ዝናም እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡



ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2026,
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች		
ክልል	ዞን	በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን
አሮሚያ	የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ሶማሌ	የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሽበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ እና ነጎብ፣ ጃረር፣ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ደቡብ ኢትዮጵያ	ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ሲዳማ ክልል	ሁሉም የክልሉ ዞኖች	መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ)
የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ዞኖች		
አሮሚያ	የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
ቤንሻንጉል ጉምዝ	የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
ጋምቤላ	የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ)
አማራ	የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም እና የአዊ ዞኖች	ቀላል መጠን ያለው ዝናብ (ከ 1-10ሚ.ሜ)
ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ	የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች	መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ)
ደቡብ ኢትዮጵያ	የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ ዞኖች	መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ)

ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎች		
አማራ	የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅ ጎጃም፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች	ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ)
አሮሚያ	የምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች	ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ)
ትግራይ	የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች	ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ)
ማዕከላዊ ኢትዮጵያ	ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ	ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ)
ሶማሌ	የሲቲ፣ ፋፈን እና ኤረር ዞኖች	ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ)
አፋር	ቀልበቲ፣ ፋንቲ፣ ማሂ፣ ሃሪ፣ ጋቢ ዞኖች	አነስተኛ መጠን
ድሬዳዋ እና ሐረሪ		ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ)

2.1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናቶች በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የዝናቡ መጠንና ስርጭት ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

በመጪዎቹ የኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም የተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ እንዲሁም በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅትን ዝናብ እያገኙ በነበሩት በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና የሰሜን የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)፡፡



ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-10/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

2.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሳምንቱ አጋማሽ ጀምሮ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በተለይም ደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በምስራቅ የሀገራችን አካባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የአፈር ውስጥ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። እንድሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው የአፈር ዉስጥ እርጥበት ያገኛሉ። በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከታች የቀረቡትን ዝርዝር ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 2)፡፡

2.3 እ.አ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኦክቶበር አስራ አንድ ቀናት በባሮ አኮቦ፣ በላይኛውና በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ እንዲሁም በላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት የሚጠበቅ ሲሆን፤ በስምጥ ሸለቆ፣ በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ በመካከለኛውና በታችኛው ገናሌ ዳዋ፣ በዋቤ ሸበሌ እና በኦጋዴን ተፋሰሶች ደግሞ ከቀላል እስከ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ይኖራል። በመሆኑም ሊኖር የሚችለውን መልካም ዕድሎችን ለመጠቀምና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለመቀነስ የሚከተሉትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳቦች መተግበር ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 3) ፡፡

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

የክረምት እርጥበት ተጠቃሚና የመኸር አምራች ዞኖች			
ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የተሰጠ ምክረ ሃሳብ**
ከኦሮሚያ የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች ከጋምቤላ የአኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ ከአማራ ክልል የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም እና የአዊ ዞኖች ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ደቡብ ኢትዮጵያ የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ ዞኖች	➢ የአፈር ውስጥ እርጥበት መሻሻል ➢ ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት እና ፍሬ ለማፍራት ➢ ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎች እድገት ➢ ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል ➢ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት ➢ ለቋሚ ተክሎች እና ለግጦሽ ሳር ዕድገት ➢ ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ	➢ የአረም መስፋፋት ➢ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት	➢ የሰብል በሽታንና አረምን አስቀድሞ መከላከል፤ ➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም ➢ አርሶ አደሮች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው ማድረግ ➢ የድጋሚ አረምን ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበርቤላ

በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች			
ቀላል መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የተሰጠ ምክረ ሃሳብ**
ከኦሮሚያ የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሶማሌ የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ እና ነጎብ፣ ጃረር፣ ዞኖች ዞኖች ሲዳማ ክልል ሁሉም የክልሉ ዞኖች፤	➢ የበጋ ተጠቃሚ ደጋማ ስፍራዎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ➢ የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ፣ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል ➢ የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም	➢ የትነት መጠን መጨመር፤ ➢ የፀረ ሰብል ተባይ መከሰት ፤ ➢ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆን	➢ የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም ➢ የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል ➢ የአፈር ውስጥ የትነት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤ ➢ ለእንስሳት የግጦሽ ሣርን በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ
• ባሮ አኮቦ • ላይኛውና መካከለኛው አዋሽ ጊቤ • ላይኛው ገናሌ ዳዋ	• የወንዞች ፍሰት መጨመርና ግድቦች የውሃ መጠን መሻሻል • የመስኖና የሃይል ማመንጫ ግድቦች የውሃ ክምችት መጨመር • የገፀ ምድርም ሆነ የከርሰ ምድር ውሃ ሀብት መጨመር • የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን መሻሻል	• ከፍተኛ ትነት መኖር	• የዝናብ ውሃ ማሰባሰብና ማጠራቀም
ከቀላል እስከ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ**
• ስምጥ ሸለቆ • ታችኛው አሞ ጊቤ • መካከለኛውና ታችኛው ገናሌ ዳዋ • ዋቤ ሸበሌ • ኦጋዴን	• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል • የወንዞችና የትናንሽ ማጠራቀሚያዎች መጠነኛ መሙላት • የገፀ ምድርም ሆነ የከርሰ ምድር የውሃ ሀብተ መጨመር	• ከፍተኛ ትነት መኖር	• ከጣራና ከመሬት ወለል የሚገኘውን የዝናብ ውሃ በተገቢ ሁኔታ ማሰባሰብ • የውሃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም

ደረቅ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ
• አባይ (በአብዛኛው) • ተከዜ • ላይኛውና መካከለኛው አዋሽ • አፋር ዳናክል፣ አይሻ • መረብ ጋሽ	• የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት አለመኖር	• ዝቅተኛ የውሃ ፍሰት • እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ እጥረት	• የሚገኘውን የውሃ ሀብት በአግባቡ መጠቀም • የሚገኘውን መጠነኛ የዝናብ ውሃ ከጣራና ከመሬት ወለል ማሰባሰብ